Nessim Al-Muhaba

ወለላዬን ተቀበሉልኝ

ልክ የዛሬ 15 ክፍለ ዘመናት ገደማ፣በወርሀ ረጀብ የዓለማችን አስደናቂ የሰርግ ሥነ-ሥርዓት ተከናወነ፤ዕመት አሚናና የተከበሩ ዐብደላህ ተጣመሩ፤ የዓለማት ብርሀን ወዲያዉኑ ተፀነሱ፤ፅንሰቱ ዕዉን የሆነዉ በዕለተ ጁሙአ/ረጀብ አንድ እንደሆነ የታሪክ ጸሀፍት ያስረዳሉ። እንዲህም ሆነና ከአድማሱ ላይ የአላህ እዝነትና በረከት ሊዘንብ አዳመነ፤ ፍቅር ለዘመናት ከተነጠቀዉ ዙፋን ላይ ዳግም የሚሰየምበት ጊዜ ደረሰ። የአላህ ችሮታ ከየትኛዉም ዘመን በላይ ሊትረፈረፍ አሰፈሰፈ፤የሰዉ ልጅ ክብር ሊመለስ፣ምድርን እንደብርድ ልብስ የሸፈናት የመከራ ጭጋግ ሊገፈፍ ጊዜዉ መቃረቡ ተበሠረ። የእመት አሚነት እርግዝና ልክ እንደበረሀ ሌሊት ምቹ ነበር። በነዚያ ጣፋጭ የርግዝና ወራት ዐጃኢበት ሲያዩ ከረሙ።

በሰማይ ቀበሌ፣በመላእክት ዓለም ዜናዉ እንደጉድ ተናፈሰ። ያ ለዘመናት ዝናዉ ሲነገርለት የኖረዉ የ‹አዘል› ጀግና ምድር ላይ ሊሰደር ጊዜዉ መቅረብ በሰፊዉ ተወራ። በአራቱም ማዕዘናት የነበሩ የሀይማኖት ሊቃዉንትና አዋቂዎች የጀግናየ ዘመን መድረሱ ተሰምቷቸዋል። ያላወቁት ነገር ቢኖር የት ቦታ ላይ ሊወጣ እንደሚችል ብቻ ነዉ። አይሁዶች ከነርሱ ዉስጥ ሊሆን እንደሚችል ገምተዋል። ከዚህም አልፈዉ ቁርአን በአል-በቀራህ ምዕራፉ ‹‹የስተፍቲሁነ›› እንዳለዉ ‹‹እርሱ ሲመጣ ተከታዮቹ ሆነን እናሸንፋችኋለን›› እያሉ በዐረብ ጎረቤቶቻቸዉ ላይ ይመጻደቁና ይዝቱ ይዘዋል።[14] ታዲያ ምን ይሆናል፤ በአዘል አልታደሉምና ‹‹ፊለማ ጃአሁም ማዐረፉ ከፊሩ ቢህ፤››[15] እንዲያዉም ቀንደኛ ጠላቶቹ ሆነዉ አረፉ። ‹‹ፊለዕነቱ ላሂ ዐለል ካፊሪን፤››[16]

[14] አልበቀራህ 89

Scanned by CamScanner

የታሪክ አዋቂዎች ‹‹ኢርሀሷት›› በማለት የሰየሟቸዉ ተአምራት በስፋት በመከሰት ላይ ነበሩ። ሸኽ ሰይድ ኢብራሂም ‹‹አል መዉሩዱ ራኢቅ›› ዉስጥ በጥቂቱ እንደዘከሩት ፅንሱ ማህጸን ላይ ያረፈ ቀን የጀሀነም በሮች ተዘግተዉ የጀነት በሮች ተከፍተዋል። መላእክት ብሥራት ተለዋዉጠዋል። እንስሳት የደስታ መልዕክት በየቋንቋቸዉ ተላልከዋል። ዐርሽና ኩርስይ በሀሴት ሰክረዋል።

ጀነት ተከፈተች ሰፍታ ተሸልማ፤
ጀሀነም ተዘጋች ደክማ ተስለምልማ፤
መሬት ኑር ተሞላች እጅግ ቀን ጪልማ፤
ባንድ ቀን ዳር ከዳር አብልጋ አስምልማ፤[17]

የወለላዬ መፀነስ ለሸይጧንና ለአጋሮቹ ትልቅ መርዶ ሆነ። ለሚሊዮኖች ዓመታት ሲፈሩት የነበረዉ አስደንጋጭ ነገር ደረሰ። የዚያን ቀን ኢብሊስ ቅስሙ በሀዘን ተሰበረ።የቀለሰዉ ጎጆ ዓይኑ እያየ መፍረሱ ነዉና የሚሆነዉን አሳጣዉ። በ‹‹ሊሳነል ሀል›› እየየዉን አቀለጠዉ። በረዥሙ የህልዉና ዘመኑ እንዲህ ዓይነት እንቅልፍ የሚነሳ መከራ አጋጥሞት አያዉቅም።

እጅግ ዘመን ኖሮ ዊሳዳዉ ቢቀርብ፤
ዓለሙን ኑር ሞላዉ ከሸርቅ እስከ ገርብ፤
የሸያጢን ቢናእ ደሰሰ ሊኽርብ፤
ከመሬት ስቀቀ ያሳንድ ቀን ሀርብ፤[18]

በርሳቸዉ መጸነስ የጥንቆላ ዓለም አከተመለት። ጅኖች ከሰማይ ወሬ ቃርመዉ ለወዳጆቻቸዉ የሚያቀብሉበት መስመር ሙሉ በሙሉ በከዋክብት ትንታግ (ሺሀብ) ተዘጋ። ‹‹ነፈሩን ሚነል ጂኒ›› ይህን

17 ሸኽ ሰይድ ኢብራሂም፣ ፈድሉ ዘላለም..መንዙማ
18 ያስፈዉ ምንጭ

Scanned by CamScanner

ዕዉነታ ሳይደብቁ አወጉን::[19] ይህ ማለት የሰዉ ልጅ የጨቅላነት ዘመን ላይመለስ ነጎደ ማለት ነዉ:: የጥንቆላ ወይም የ'ኩራፋት ዘመን ተጠናቆ የአይምሮ ሚና ነገሰ ማለት ነዉ:: ‹‹ሊቀዉሚን የዕቂሉን›› እያለ ባለ አዕምሮዎችን የሚያናግር፣የዕዉቀትን ደረጃ ከፍ ከፍ የሚያደርግ መልዕክት ከሰማይ የሚወርድበት ሰዓት ተቃረበ ማለት ነዉ:: የሰዉ ልጅ በጥሞና ማሰብ ሲጀምር ኢብሊስና አጋሮቹ ወዮላቸዉ:: የነርሱ መግቢያ በር መሀይምነትና ሻህዋ ናቸዉና እንዲያስተነትን ፋታ አይሰጡትም፤ በተለያዩ አልባሌ ነገሮች ጠምደዉ እንደልባቸዉ ያርሱታል:: አዲሱ እንግዳ ግን የሻህዋን እግረ ሙቅ በጥበብ ይበጣጥሳል፤አዕምሮን ከአንጉልና መረጃ አልባ አስተሳሰቦች ነጻ ያወጣል፤ ከእንግዲህ ዕምነቶች ‹‹ሀቱ ቡርሀነኩም››[20] በተሰኘ ጠንካራ ሚዛን ይፈተሸሉ፤ይህን ሚዛን ያላለፉት ያለርህራሄ ዉድቅ ይደረጋሉ:: ሻህዋ በአዕምሮ ልጓም ተይዞ ለታለመለት ዓላማ ብቻ ይዉላል:: ሸርክ በተዉሂድ፣መሀይምነት በአብርሆት ይተካሉ:: የሰዉ ልጅ ከአምላኩ የነጠለዉን የጃሂልያ ሸለቆ በአስደማሚ ሁኔታ ይሻገራል:: የአስካሪ መጠጥ ጋኖች ይሰበራሉ:: የዝሙት ሸንኮፍ ከማህበረሰቡ ይነቀላል:: ግንባሮች ለአላህ ብቻ ይደፋሉ:: ልቦች እርሱን ብቻ ይፈራሉ:: ደም የተቃቡ ሁሉ እርቀ ሰላም አዉርደዉ በጥልቅ የወንድማማችነት ስሜት ይተሳሰራሉ...::

በአዲሱ እንግዳ ትጋት ይህ ሁሉ እንደሚሆን ኢብሊስ ጠንቅቆ ስለሚያዉቅ እርሳቸዉ የተጸነሱ ዕለት ምድር ቁና ብትሆንበት አይገርምም:: ከሁሉ ከሁሉ ግን የርሳቸዉ መከሰት ከቂያማ ትልልቅ ምልክቶች መካከል አንዱ መሆኑን ማወቁ የበለጠ ስቃይ ሆኖበታል:: ቢችል ዕንሱን ከማህጸን ዉስጥ እንዳለ ቢያፈርሰዉና ቢያመክነዉ ምኞቱ ነበር:: ግና ወለላዩ በቀደር ጥበቃ ሥር ናቸዉና ምኞቱ ወደተግባር

[19] አልጂን 8-9
[20] አልበቀራህ ιιι

Scanned by CamScanner

ፈጽሞ ሊለወጥ አይችልም። እናም በሀዘንና በስጋት ከመንቀራጠጥ በስተቀር ሌላ የሚያደርገዉ ነገር አልነበረም።

በጥቅሉ የፍቅሩ ንጉስ ከእናታቸዉ ማህጸን ዉስጥ ካረፉበት ዕለት አንስቶ በዓለም ላይ የለዉጥ ንፋስ መንፈስ መጀመሩ ያስታዉቃል።

ዙሪያዉን ነፋፈሰ፤
በምርቱ እየታፈሰ፤
በጁዱ ተነፈሰ የኻሲቃችን ቁድራ
(የጁዱ ቡሽራ የዉጁዱ ሙሽራ)[21]

ወራት እንደጅረት ዉሀ እየፈሰሱ አለፉ። የዓለማት ብርሀን መወለጃ ቀን ደረሰ። ረቢዐል አወል 12ኛ ምሽት፤ እመት አሚነት ምጥ ጀመራቸዉ፤ ሂደቱ ተፋፋመ፤ የዓለም የፍቅር ንጉስ ከ‹‹ገይብ›› ወደ‹‹ሹሁድ›› ሊዘልቁ ተሰናድተዋል፤ በምናብ ወደኋላ መለስ ብለን ከዚያ ቅጽበት እንሳተፍ፤ እኔ በምናብ ብዙ ጊዜ ተሳትፌያለሁ። ያን የተላቀ ጎጆ ከከበቡ የንጉሱ ቤተሰቦች ጋር ሆኜ ጭንቀታቸዉን ተጋርቻለሁ። ከእናታችን ጋር እኩል ተንበርክኬ በሀሳብ አምጫለሁ። አሁን የሆነ ያህል እየተሰማኝ በጉጉት አፈን ከፍቻለሁ፤

የመካ ከተማ የአዲሱን እንግዳ ልቅናና ሚስጥር በሚያዉቁት ወራጅና ወጭ የሰማይ መላእክት መጨናነቋ ዕሙን ነዉ። የዚያን ቀን እንግዳ በዝቶባታል። እስትንፋስ ቀጥ ያደርጋል፤ከሥፍራዉ ተገኝተዉ ያችን ቅጽበት ያዩ ታድለዋል። እኛ ሀበሾችም በአሳዳጊያቸዉ በኡም አይመን /በረካ/ ተወክለን የዚህ አስደናቂ ትእይንት ተሳታፊዎችና የዓይን እማኖች ስለሆንን ለአላህ የከበረ ምስጋና ይድረሰዉ። ይህን ዕድል ያገኘ ከመካዉያንና ከኛ በስተቀር ሌላ ዘር በምድር ላይ የለም። የዚህን መመረጥ አንደምታ በየፊናችሁ መርምሩት።

[21] ሸኽ ሰደድ ኢብራሂም፤የጁዱ ቡሽራ..መንዙማ

Scanned by CamScanner

እመት አሚነት ጥቂት እንዳማጡ ለሚሊዮኖች ዓመታት ሲጠበቁ የኖሩት መድህን ተወለዱ፤ሰይድ ቂሌ ይህን አስደማሚ ሁነት እንዲህ ገልጸዉታል፡-

ከዉኑ ተንተግትጎ በኑር ሲጥበረበር፤
አሚነት ስታምጥ ተስኗት መሶበር፤
አላህ ማዝለቅ ቢሻ የሹኡኑን ኸበር፤
ሰኞ ወለደችዉ አብርቶ አንደጀንበር፤[22]

እነሆ የረሀመቱ ንጉስ ተወለዱ። በያላችሁበት እልል በሉ፤ቁርአን ‹‹ፈልየፍረሁ››[23] ብሎን የለ፤ከዚህ በላይ ምን ደስታ አለ? ከዚህ በላይ ምን ጸጋ አለ? ታላላቅ ዑለሞች ይህን ዜና እንደዋዛ አያልፉትም። ‹‹ዉሊደል ሙስጠፋ ወሀቀል ሀናኡ›› የሚል ብስራት በሰሙ ቁጥር አዲሱን እንግዳ ለመቀበል ከመቀመጫቸዉ ይነሱና ‹‹መርሀባ ነቢ መርሀባ›› በማለት መልካም ምኞታቸዉን ይገልጻሉ። እናቶቻችንም እልልታዉን ያቀልጡታል። እኔም ፅሁፌን አቋርጬ ከመቀመጫየ ተነስቻለሁ። መርሀባ ወለላየ፤መርሀባ ሙስጠፋየ፤መርሀባ ሸፈዐየ፤ መርሀባ መርጊያየ፤መርሀባ ማረፊያየ። እሰየዉ፣ እንኳንም ተወለዱልን፡ ፡ እሰየዉ፣እንኳንም እርስዎን ለኛ፣እኛን ለርስዎ አላህ መረጠልን።

Nessim Al-Muhaba

22 ሸኽ ሰደድ ኢብራሂም፣ፈድሉ ዘላለም...መንዙማ
23 ዩኑስ 58

Scanned by CamScanner